# “የንጋት ወፍ ጥሪ”

ማለዳ ማለዳ ሳይነጫነጭ ከእንቅልፉ የተነሳበት ቀን አልነበረም። ተከራይቶ ከሚኖርበት ክፍል በግራና በቀኝ የሚያጎራብቱት ሁለት ሰዎች በሕግ የተመደቡለት ከእንቅልፍ የማንቂያ ደውሉ ይመስላሉ። ከእርሱ መኝታ ቤት በስተግራ በቅርቡ ሐይማኖቷን ከኦርቶዶክስ ወደ ‘ጴንጤ’ የቀየረች ሴት ድምጿን ከፍ አድርጋ የምታሰማው የማለዳ ጸሎት፥ በቀኝ በኩል ደግሞ የሴትዮዋን ጸሎት ላለመስማት የሙዚቃውን ድምጽ ከጣራ በላይ እያስጮኸ የሚዘፍን ማንአለብኝ ባይ የባንክ ገንዘብ ከፋይ ገና ጎህ ሳይቀድ ከእንቅልፉ ያባንኑታል። እዚያ ላይ የቤት አከራዩ ላም ማለዳ የምታሰማው ጥጃዋን የመናፈቅ ይሁን፥ የወተቷን መታለብ ለመቃወም የምታሰማው ድምጽ ሌላኛው ሳይወድ በግድ ከእንቅልፉ የመንቂያ ደወሉ ነበር።

ዛሬ ግን ከእንቅልፉ ያባነነው የእሳት አደጋ መኪና ያንን “መጣሁላችሁ!” የሚል ማስጠንቀቂያውን እያወጀ በአካባቢው ሲያልፍ ነው። ዐይኑን በግድ ለመግለጥ እየታገለ አልጋው ዳር ላይ ተቀመጠ። እግሩን ወደ ወለሉ ሰድዶ ነጠላ ጫማውን ፈለገው። አላገኘውም። ማታ የት እንደወረወረው አያስታውስም። ተኝቶ እንዳረፈደ ገብቶታል። እንዴት በዛሬው ቀን ተኝቶ ያረፍዳል? በዛሬዋ ልዩ ቀን! በራሱ ላይ እንደመናደድ እያደረገው ሠዓቱ ስንት እንደኾነ ለማወቅ ከወገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ ከአልጋው ፊት ለፊት ወዳለው መጽሐፍ መደርደሪያ አመራ። ሶስት ሰዓት ተኩል ይላል። እንደፈራው አርፍዷል። ልብሱን በፍጥነት ለባብሶ ጫጩቶቿ የተነኩባት ሠጎን የምታባርረው ይመሥል እየተከለፈለፈ በአፍሪካ ጎዳና በኩል ወደ አብዮት አደባባይ አቅጣጫ ገሰገሰ።

ድካም ይጎበኛቸው የጀመሩ ረዣዥም ቅልጥሞቹ የልቡን ፍጥነት መሻት ባያረኩለትም እንደአቅማቸው ጎዳናውን አፈስ አፈስ እያረጉለት ወደ ፊት ያስፈነጥሩታል። የፍላሚንጎን ሬስቶራንት እንዳለፈ፥ ነጭ የለበሱ ምዕመናን የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያንን ደረጃ ሲወጡ እና ሲወርዱ ቆም ብሎ ለአፍታ አስተዋለ። አንገቱን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አቅጣጫ ሰበር አድርጎ አማተበና “በቀኝ አውለኝ ምቀኛ ሽረኛውን አንተ ያዘው አባቴ” ብሎ ለቅዱስ እስጢፋኖስ ተናግሮ ወደ ፊቱ ገሰገሰ። የአዲስ አበባ ስታዲየምን በስተግራው ትቶ በጀርባ በኩል ወደ ቸርችል ጎዳና ወጣ።

ፍጥነቱን ቀነሰ። በግንባሩ ላይ ላቡ ቸፈፍ ማለቱን የታወቀው የቸርችልን ጎዳና ይዞ ወደ ራስ ሆቴል አቅጣጫ ረጋ ብሎ ሲራመድ ነው። ከዘርፋፋ ኮቱ የግራ ኪስ ሠማያዊ መሀረብ አውጥቶ የፊቱን ላብ ጠረግ እያደረገ ከራሱ ጋር ፈገግ እያለ። ዛሬ መልካም ቀን እንደኾነ ታውቆታል። ሮሃ ካፌ ዛሬ ትደምቃለች። ለመጨረሻ ጊዜ

የግጥም ምሽት በሮሃ ካፌ የተደረገው መቼ እንደነበር በቅጡ ትዝ አይለውም። አሥር አመት ሳያልፈው አልቀረም። አንጋፋ እና ታዋቂ ገጣሚያን÷ ቤት ያፈራቸው ጎያስያን፤ ወሬ አባራሪ ጋዜጠኞች÷ ብሔራዊ ቲአትር ውስጥ ማለዳ ማለዳ ጸሀይ ሲሞቁ የሚያያቸው ቲአትረኞች ሁሉ ይመጣሉ። "ሁሏም ትመጣና ወይ ግጥሟን ታነባለች ወይ ታሽሚጥጣለች" አለ ለራሱ።

ራስ ሆቴልን ሲደርስ ይበልጥ ፍጥነቱን ቀነስ አድርጎ መራመድ ጀመረ። እጆቹን ወደ ሸሚዙ ልኮ የኮሌታው ጫፎች ከላይ በደረበው ሹራብ ሥር በትክክል መሸጎጣቸው ፈተሸ። ቦታቸውን ይዘዋል። ወደ ጫማው ተመለከተ። ጫማው አልተወለወለም። ከዋናው መንገድ ማዶ ተደርድረው የማለዳ ፀሐይ ከሚሞቁ ሊስትሮዎች ውስጥ አንዱን እጁን አወዛውዞ ጠራው። እድሜው ከአስራዎቹ አጋማሽ የሚጠጋ ሊስትሮ እየተንደረደ መጣ። ሊስትሮው ዐይኑን የውብሸት ጫማ ላይ ተክሎ አጠገቡ ሲደርስ የሊስትሮ እቃውን ዘርግፎ መሬት ላይ በእንብርክኩ ቁጭ ብሎ ጫማውን ማሳመር ጀመረ። ውብሸት ጫማዋን የሊስትሮው ሳጥን ላይ አስቀምጦ በሀሳቡ ሮሃ ካፌ ውስጥ ስለሚከወኑ ነገሮች እና ማታ ስለሚያደርገው አጠር ያለ ንግ ግ ር እያሰበ ለአፍታ በሀሳብ ተወሰደ።

* * *

ያለፈው ሳምንት ማክሰኞ ነው ነገር ሁሉ እንደገና የተጀመረው። አንድ ፀጉሮን ያንጨባረረ ጥቁር ÷ ቀጭን ወጣት ወደ ሮሃ ካፌ መጣና በሩ ጋር ቆመ። ውብሸት በወረደ ቡና ማኪያቶ ለራሱ እየሠራ ነበር ለራሡ። "ምን ይገትርኻል? ወይ ግባ ÷ ወይ ወደ ግራህ÷ ወይ ወደ ቀኝህ ሂድ" አለው ገበያቸው ወደ ደራው "ሸገር"ና "አራዳ" ካፌ እየጠቆመው። ወጣቱ የውብሸትን ንግግር ችላ ብሎ ለአፍታ በሩ ላይ ቆመና፤

"ገጣሚ ውብሸት" ብሎ ጠራው።

ውብሸት የሚሠራውን ማኪያቶ ገታ አድርጎ ለአፍታ ቆም ብሎ ወጣቱ ላይ አተኮረ። ማንም "ገጣሚ ÷ባለቅኔ" ብሎት አያውቅም እስከዛሬ።

"ያልታደልክ! ይልቅ ያንን የግጥም ምሽት አስጀመረው፤ ሞያ መስሎኻል አንድ መጽሐፍ ጽፎ÷ መጽሐፍ ሲያቃጥሉ መኖር" ብሎት መልስ ሳይጠብቅ ጥሎት ሄደ።

ይህ ወጣት ማን እንደኾነ÷ ማን እንደላከበትም አያውቅም። ውብሸት ካፌውን ዘግቶ ማታውኑ እግሩ ወደ መራው አቅጣጫ በእግሩ ሲኳትን አመሸ ፤ስለ ሮሃ ካፌ መልካም ዘመናት እያሰበ። ምን ዓይነት ደግ ጊዜ ነበር! ባለፉት አሥር ዓመታት ምን ሠራ ÷ ምንም። አንድ የጻፋትን መጽሐፍ እንደ መስቀል ደመራ ሲያነድ ኖረ እንጂ ምን ሠራ? ራሱን ከግንብ ጋር ቢያጋጭ በወደደ።

ውብሸት መስፍን “የንጋት ወፍ ጥሪ” የሚል ርእስ ያለው የግጥም መጽሐፍ አሳተመና የኀያስያን፥ አንጋፋ እና ጀማሪ ገጣምያን መቀለጃ ኾነ። ስለ ወፍ ነበር የጻፈው። አንዲት ወፍ ነበረች። እንደመስቀል ወፍ የአደይ አበባ ፍካትን ተከትላ በአመት አንድ ጊዜ የማትመጣ። ሠማዩ የአህያ ሆድ ሲመስል “አለሁ ፥ አለሁ” እያለች የአዲስ አበባን ንጋት ስለምታውክ ወፍ። አንድ ቀን ወፎቹ ሁሉ የእርሷን ድምፅ ኮርጀው ከእርሷ እኩል “አለሁ አለሁ” እያሉ መጮኽ ጀመሩና ዜማዋን ቀሟት። በዚያው ጠፋች ወፏ። ወደ አዲስ አበባ አልተመለሰች። ‘የት ገባች ወፊቱ?’ አለና ጻፈ።
መጽሐፉ ለገበያ ሲቀርብ የኀያስያን መዘባበቻ ኾነና አረፈው። “በጥበብ ላይ የሚቀልድ እንቶፈንቶ” ተብሎ እንደ አርዮስ ከተወገዘ ያለፈው ሳምንት ማክሰኞ አሥርኛ ዓመቱ ነበር።

ግጥሞቹን የጻፈው “ሮሃ ካፌ” የአዲስ አበባ ቁጥር አንድ የጥበብ መዳረሻ ማዕከል ተደርጋ በምትቆጠርበት ጊዜ ነበር። ግሩም ጊዜ ነበር ለጥበብ እና ለሮሃ። ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ በዋሽንትና በክራር የታጀበ የግጥም ንባብ ፥ በየአስራአምስት ቀኑ ደግሞ ታዋቂ የጥበብ ሰው እየተጋበዘ ውይይቱ ይጦፍ ነበር።

መጽሐፉ የታተመ ሳምንት በወጡት ጋዜጦች ላይ ኀያሲያን የብዕር ጦራቸውን መዝዘው ተገተጉት። መጽሐፉ በወጣ በአምስተኛ ቀን ማለዳ ሮሃ ካፌን ለመክፈት ማልዶ ሲደርስ የካፌው በረንዳ ላይ መጽሐፉ ተቀዶ ተጥሎ አገኘ። ይህ ሁሉ ውርጅብኝ ይመጣብኛል ብሎ ፈፅሞ አልጠበቀም። ሮሃ ካፌን ያጨናንቅ የነበረ ባለቅኔ፥ ገጣሚ ፥ኀያሲ፥ ጋዜጠኛ ሁሉ እልም ብሎ ጠፋ።

ሮሃን ካፌ ዘግቶ ለሁለት ሳምንት ከአካባቢው ተሠወረ። የውብሸት መሸሸ ተሰማና የከተማው የአፍታ ወሬ ኾነ። ድሬዳዋ ነበር የሄደው። ሲመለስ ግጥም የሚባል ጠልቶ፥ በካፌው ውስጥ ይደረጉ የነበሩ የጥበብ ዝግጅቶችን በሙሉ አቆመ። የካፌው ግድግዳ ላይ ተጽፈው የነበሩ አጫጭር ግጥሞችን አስጠፋ። ከማንኛውም ገጣሚ፥ ኀያሲ ጋር ያለውን ግንኙነት አቁሞ “የንጋት ወፍ ጥሪ” የሚለውን መጽሐፉን መጭው ትውልድ ፈፅሞ እንዳያስታውሰው ከአሳታሚዎች፥ ከአከፋፋዮች፥ ከመፅሐፍ ቸርቻሪዎች መልሶ እየገዛ ማቃጠል ሥራዬ ብሎ ያዘው።

ሮሃም ቅዝቅዝ ወዳለች፥ ቡና እና ማኪያቶ ብቻ የሚሸጥባት ካፌነት ተቀየረች። በተለይ በግራና ቀኝ የሚያጎራብቱት “አራዳ” እና “ሸገር” የተባሉት ካፌዎች ከተከፈቱ በኋላ ሮሃ ዝናዋ እየተረሳ መጣ። ውብሸት ሮሃ እያስተዳደረ መቆየት የሚፈልገው ያሳተማቸውን መጽሐፍት አንድዶ እስኪያቃጥል ድረስ ብቻ ነበር።

ዘጠኝ መቶ ሃምሳ መጽሐፍ ነበር ያሳተመው። ከድሬዳዋ በተመለሰ በወር ከሃያ ቀን ውስጥ ዘጠኝ መቶ ሠላሳውን መጽሐፍ ገዝቶ አነደደው። የቀሩትን 20 መጽሐፍት መፈለግ ግን ከአስር አመት በላይ ፈጀበት። መጽሐፍቶቹን ማን እንደገዛቸው ስለማያውቅ በየአሮጌ መጽሐፍ መሸጫ መደብሩ ሲያስስ ኖረ። ብዙ ጊዜ የሥራ መውጫ ሠዓት ጠብቆ "የንጋት ወፍ ጥሪ የሚባል መጽሐፍ ያለው!" እያለ ይጠይቅ ነበር። እንዲያም ኾኖ እስካለፈው ሳምንት ማክሰኞ ድረስ ከሃያው ፍሬ መጽሐፍ አሥራ ስድስቱን በስንት ልፋት ገዝቶ ማንደድ ችሎ፤ አራት መጽሐፍ ብቻ ይቀረው ነበር።

ከማክሰኞ ጀምሮ ግን የአሥር አመት ልፋቱን ትቶ እንደገና ወደ ጥቡብ ለመመለስ የመጀመሪያውን ታላቅ የግጥም ምሽት ለማሰናዳት ዝግጅቱን አጧጧፈ። ማስታወቂያ በየሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ተለጥፈዋል። ስለ ምሽቱ ይዘት ለጋዜጦች ማብራሪያ ልኳል። ሲያስጨንቀው የነበረው እንግዳ እንዳይበዛ ብቻ ነበር።
* * *
ለሊስትሮው አንድ ብር ሰጥቶ መልስም ሳይጠብቅ ወደ ካፌው በርጋታ አመራ። አዲስአቤ' "ከተት!" የተባለ ይመስል ከየጓዳው ነቅሎ በረኸሙ ብሔራዊ ቲአትር ተቆጣጥሮ ቡና፣ ሻይና ማኪያቶ እየጠጣ ያውካካል። የእርሱ ካፌ ስላልተከፈተ በረንዳው ላይ ተኮልኩሎ ቡና ÷ማኪያቶውን የሚልፈው ደምበኛ የአራዳ እና ሸገር ካፌዎችን ገበያ ብቻ እያደመቀ እንደኾነ ታሰበውና ቅናት ቢጤ ወረር አረገው። ወዲያው መልሶ "ስማ ውብሸት መስፍን! አንተ ባለቅኔ እንጂ ነጋዴ አይደለህም! ለምን ወርቅ አይቸበችቡም" አለና ራሱን ገሠፀው። የካፌውን ቁልፍ ለመፈለግ ወደ ኪሱ ገባ። መጀመሪያ ወደ ግራ ኪሱ። ሠማያዊ መኅረብ አገኘ። ቀጥሎ ሌሎቹን ኪሶቹን አራገፈ። የካፌውን ቁልፍ ቤት ረስቶት ሳይመጣ አልቀረም። ቁልፉን ረስቶታል። በልበ ቢስነቱ ራሱን እየረገመ ወደ ካፌዎቹ ተጠጋ። የከተማው ቡና ወዳጅ ሁሉ በአዋጅ የተጠራ ይመስላል። የሚሰማው የስኒ እና የማንኪያ ኳኳታ÷ የቡና ጠጪው መቅበዝበዝ÷ የአስተናጋጆቹ መለስ ቀለስ ማለት ካፌዎቹን የእብድ ገበያ አስመስሏቸዋል።

ውብሸት ወደ ካፌዎቹ ተጠጋ። አራዳ ካፌ ይታየዋል። ሸገር ካፌም ይታየዋል። ሮሃ ካፌ ግን አይታየውም። ይበልጥ በቀረበ ቁጥር ግራ እየተጋባ÷ የሚያየውን ነገር ለመቀበል እየተቸገረ ወደ ካፌዎቹ በረንዳ ደረሰ።ወንበሮች ተይዘዋል፤ ገሚሱ ቆሞ ስኒውን ያጋባል። በረንዳ ላይ የተደረደሩ ወንበሮች በሙሉ ተይዘዋል። ሮሃ ካፌ እዚህ ነበር።
ሮሃ ካፌ ግን በቦታው የለም።
የሚያየው ነገር በሙሉ ውሸት እና በውኑ እንዳልኾነ ራሱን ለማሳመን ይታገላል።

ካፌው የለም።

“ሮሃ ካፌ” እስከ ትላንት ማታ አምስት ሰዓት ድረስ በ “አራዳ” እና በ “ሸገር” ካፌዎች መካከል ይገኝ ነበር። የሚያየውን ነገር ለመቀበል ተስኖት በዝምታ ተውጦ ዐይኑን እያስለመለመ የብሔራዊ ቴአትርን በረንዳ ደገፌው ካቆሙ ምሰሶዎች አንዱን ተደግፎ ከሃያ ደቂቃዎች በላይ እንደጅብራ ተገተረ፤ ዐይኖቹን በረንዳ ላይ ተደርድረው ቡና የሚጠጡ ስዎች ላይ እያንከላወሰ። ቡና የሚጠጡትን ሰዎች አንድ በአንድ በእርጋታ ምስላቸውን በአእምሮው መዘገባቸው።

የካፌዎቹ መግቢያ በር የውጭ ግድግዳ ላይ የተጻፈውን የካፌዎቹን መጠሪያ ስም በርጋታ አነበበው። “አራዳ ካፌ” ይላል አንደኛው። የዐይኖቹን ብሌን ከግድግዳው ላይ ሳይነቅል ወደ ሚቀጥለው የካፌ በር አናት ላይ ሸርተት አደረጋቸው። “ሸገር ካፌ” ይላል ቀጥሎ ያለው።

“እንዴ! የምር ነው እንዴ ይሄ ነገር?” አለ ለራሱ።

መልሶ ደግሞ “ሞኝ ነህ እንዴ አንተ ደግሞ!? የማይሆን ነገር ነው!” ሲል ራሱን ገሰፀ። ፊቱን ከካፌዎቹ አዙሮ ከቆመበት ፊት ለፊት የሚገኙ ሕንጻዎችን ተመለከተ። “አዲስ ካፌ”ን በርቀት ተመለከተው። ትክክል ነው። ቦታ አልሳተም። ላለፉት አሥራ አምስት አመታት ሲመላለስበት የኖረው ቦታ ነው። ወዲያው ደግሞ በሀሳብ ከነጎደበት መለስ ብሎ “ሮሃ ካፌስ የት ሄደ?” አለ ራሱን እንደመሞገትም፥ ማንቡብ እና ማየት ባለመቻሉ ራሱን በሀሳብ እየኮረኮመው።

“ዐይኔ ማንቡብ አቋሚል ማለት ነው” አለና ከቆመበት ከብሔራዊ ቴአትር ሕንጻ ሥር ተነስቶ ወደ ራስ ሆቴል አቅጣጫ ተራመደ። ራስ ሆቴል ዋና መግቢያ በር ትይዩ ላይ ሲደርስ ቆመ። ዐይኖቹን አሸት አሸት አደረገና በዙሪያው የሚያልፍ የሚያገድመውን፥ የሚካለበውን፥በርጋታ የሚያዘግመውን ፍጡር ሁሉ በሕልሙ ሳይኾን በውኑ የሚያየው ፥ የሚገነዘበው ትዕይንት መኾኑን ለራሱ ደጋግሞ ነገረው። ተንጠራራ። በሁለቱ እጆቹ መዳፍ ግንባሩን መታ መታ አደረገ።

ከራስ ሆቴል እስከ አራዳ ካፌ ያለውን ከአርባ ሜትር የማይዘል መንገድ በርጋታ እየተራመደ ወደ ካፌዎቹ አዘገመ። “ምን ነካኝ...!” አለ ራሱን። “ሆሆይ!... ዐይኔ ብሎ ብሎ ማየት እንኳን ይቸግረው! እርጅና መጣች ማለት ነው” አለ። “ዐይኔ ባይሆንስ?” የሚል ነገር መጣበት ደግሞ። ማበድ መዘንጋት ጅምሬ ይሆን እንዴ?” ራሱን ጠየቀ። አላበድኩም። አለባበሱን ተመለከተ። ደህና ነው። ባልሸቀረቀርም ራሴን አልጣልኩም አለና ራሱን አጽናናው። መቼም በዚህ ዘመን ካፌው ከዚህ ቦታ ተነቅሎ ጠፋ ብል እብድ ይሉኛል እንጂ ማን ያምነኛል እያለ በርጋታ መጓዝ ጀመረ። አጭሩ ርቀት ዘላለም እንዲወስድበት እየተመኘ። ከራሱ ጋር እየወራ ወደ ካፌዎቹ ተመለሰ። ዐየ። አሁንም ሮሃ ካፌ በቦታው ፈጽሞ የለም። “እንዴት አንድ ሰው እንኳን ትላንት

ማታ ድረስ እዚህ የነበረው ሮሃ ካፌ የት ሄደ ብሎ አይጠይቅም?” አለና በረንዳ ላይ ተኮልኩሎ የለ ሀሳብ ቡና የሚጠጣውን ደንበኛ ሁሉ በትዝብት ገረመመው።

ምን ማድረግ እንዳለበት ማሰብ ጀመረ። “ይጮኽ? ካፌዬ ካፌዬን ዘረፉኝ ይበል? እንደዚያ ካለማ ‘እብድ ነው ብለው’ ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ሊልኩት ነው። ዝም ማለት አይችልም። ራሱንስ ምን ብሎ ሊያሳምነው፥ በምን ሊተዳደር ነው?” በጥያቄ እንደተወጠረ የሚያውቃቸው ሁለት የመድን ድርጅት የሂሳብ ሠራተኞች ሠላምታ ሳይሰጡት ወደ ሸገር ካፌ ሲገቡ አየ። አይተውታል። ፊት ለፊትም ተፋጠዋል እንጂ። እንደማያውቁት ሆነው አለፉት። እንደመናደድ አደረገው። ዐይኖቹን አንድ ጊዜ ወደ ሸገር ፥ ሌላ ጊዜ ወደ አራዳ ካፌ እያንከራተተ ሮሃ ካፌ ከጠፋበት ዓለም እንዲመለስ ተዓምር ተስፋ ያደርግ ጀመር።

ከአፍታ ቆይታ በኋላ ሁለት የሚያውቃቸው ወይዛዝርት ሠላምታ ሳይሰጡት ወደ አራዳ ካፌ ገቡ። “ምን ስለኾንኩ ነው የእግዜር ሠላምታ እንኳን የሚነፈገኝ” ብሎ ሊጋፈጣቸው ፈልጎ ነበር። መቼም ‘ለምን በግድ ሠላምታ አልሰጣችሁኝ አይባል’ አለና ዐይኖቹን ሮሃ ካፌ ትላንት ማታ ድረስ ወደ ነበረበት ቦታ መለሰ። ትንፋሹን ውጦ ዐይኖቹን ባለማመን ስሜት አንድ ጊዜ ወደ አራዳ ካፌ ሌላ ጊዜ ወደ ሸገር ካፌ እያቅበዘበዘ የረዥሙን የብሔራዊ ቲአትርን ሕንጻ ምሶሶ ተደግፎ ቆመ። የንዴት እና የመደናገር ላብ በግንባሩ ቸፈፍ እያለ እያለ መውረድ ጀምሯል። በሰማያዊ ማኅረቡ ፊቱን ያደራርቅና መኅረቧን ወደ ኮቱ ኪስ ይከታትና አፍታም ሳይቆይ መልሶ ለተመሳሳይ ሥራ ወደ ግንባሩ ይልካታል።

አጭሯ የ“አራዳ ካፌ” አስተናጋጅ ወደ እርሱ አቅጣጫ መጣች። አጭር ፀጉሯን ወደ ኋላዋ አስይዛዋለች። የለበሰችው ሰማያዊ የሥራ ልብስ ዳሌዋ ላይ ልክክ ብሎ የዐላፊ አግዳሚውን ዐይን ያደናቅፋል። ውብሸት ፈገግታዋን ይወደው ነበር፤ ቁርስ፥ ምሳ ፥ ራት የኾነ ቆንጆ ፍልቅልቅ ፈገግታ። ጥሩ ሠላምተኛው ነች። ለፈገግታዋ ግጥም ለመጻፍ ሞክሮ ምንም ስንኝ ሊፈስለት አልቻለም ነበር።

ያልደመቀ ፈገግታ እያሳየችው “ይቅርታ ጌታዬ ከቅድም ጀምረው እዚህ ጋር ቆመዋል? ምን ላምጣልዎ?”አለችው። እንደማታውቀው ኾነች እርሷም። ቅኔ ሊቀኝለት የተመኘው ያ ፈገግታዋ ቁጥብ ብሏል። ውብሸት ጠጋ ብሎ ድምፁን ቀነስ አድርጎ ተጠጋት።
“አታውቂኝም እኔን?” አላት ውብሸት። አጭሯ አስተናጋጅ ውብሸትን በትህትና አስተያየት በአንክሮ ለማስተዋል እየሞከረች ጭንቅላቷን በአሉታ ነቀነቀች።
እስኪ ተመልከቺኝ። ዐየችው።

“አታውቂኝም?” ደግሞ ጠየቃት።

“እንጃ ረስቼዎት ይሆናል ይቅርታ። የኛ ሥራ ከስንቱ ያገናኘናል፥ ስንቱን ሰው እናስታውሰው” አለች።

“እኔን ግን ታውቂኝ ነበር በደንብ? ”

መልሳ አየችው። ራሷን ነቀነቀችና።

“...ምን ላምጣልዎ አሁን” አለችው።

“ምንም አልፈልግም” ።

“ያለ ሥራ መቆም አይቻልም፥ ወይ ይዘዙ፥ ወይ ይሻገሩና ይቁሙ። ቦታውን ደንበኛ ይፈልገዋል። የቤቱ ፖሊሲ ነው”።

ውብሸት ተናደደ።

“እንዴት አንቺ! በገዛ ካፌዬ በረንዳ ላይ እንዳልቆም የሚከለክለኝ ማነው?” ብሎ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ። ይህን ነበር የፈራው።

“እሺ ሮሃ ካፌ የት ሄደ ልትይ ነው?”

“የምን ሮሃ ካፌ ነው?” አለች ግራ የገባት መስላ።

“ካፌዬ ነዋ! ሮሃ ካፌ!እዚህ ነበር ትላንት ማታ”። በረንዳ ላይ የተቀመጡት ደንበኞች ጆሮዎቻቸውን አቅንተው የውብሸት መስፍንን ጩኸት ያዳምጡ ጀመር። የሁሉም ዐይኖች እርሱ ላይ እንደ ጃርት እሾህ ላዩ ላይ ተሰግስጎበታል። ለምን እንደእዚያ እንደሚያፈጡበት አልገባውም። ‘ስንት ዘመን የለፋበት ካፌ በአንድ ምሽት እልም ብሎ ሲጠፋ!’ ካፌዬ የት ሄደ ብሎ መጠየቅ አይችልም እንዴ? ሙብቱን መጠየቅ አይችልም እንዴ?

“አሥር አመት ሙሉ ስገባ ስወጣ የኖርኩበት ካፌ የለም ስትይ አታፍሪም? እስኪ ከሜክሲኮ አደባባይ እስከ አምባሳደር፤ ከለገሀር እስከ ፒያሳ ያለ የአዲስ አበባ ሰው ይጠራና ሮሃ ካፌ የት እንደነበር ይጠየቅ? ውሸት ምን ይሠራል!?”

አጭሯ አስተናጋጅ ውብሸትን በቆመበት ትታ አዲስ የመጣ ደንበኛ ትእዛዝ ልትቀበል ሄደች። ለብቻው ‘ጉድ እኮ ነው ጎበዝ፥ ጉድ እኮ ነው’ እያለ ያጉተመትማል። የሰዉ ዐይኖች እርሱ ላይ እንደተተከሉ ናቸው።

“ወገን እንዴት ነው ምታዩኝ፥ ያበድኩ መስሏችሁ ወይ ውሸት የማወራ መስሏችሁ ? እርሱ ምስክሬ ነው እውነት እንደማዋራ!” አለ እጆቹን ወደ ሠማይ እየጠቆመ።

“የምን ካፌ ነው ጌታው?’ ብሎ ጠየቀው ከውብሸት አጠገብ ብዙም ሳይርቅ በሎሚ የተፈላ ሻይ የሚያማስል ረዥም ወጣት።

“ካፌዬ ነዋ፥ ሮሃ ካፌ። እዚህ ነበር ትላንት ማታ ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ድረስ” አለ። “አሁን ስመጣ አጣሁት። የት ሄደ ይባላል?” አለ ድምፁ ለሁሉም እንዲሰማ አድርጎ እየመለሰ።

“ቦታ ተሳስተው እንዳይሆን? ይህው ሁለት አመት ሙሉ ስመላለስ አንድ ቀንም ሮሃ ካፌ የሚባል እዚህ ቦታ አልነበረም” አለ ወጣቱ የሻይ ብርጭቆውን ጫፍ በማንኪያው እየቆረቆረ።

ውብሸት ተናደደ።

“ምን ይላል ይሄ!? እኔ ትላንት ውድቅት ሌሊት ድረስ እየደከምኩበት ነበር ስልህ፥ እንዴት ያለ ነገር ነው?ስንት ዘመን የተዳደርኩበት፥ ስንቱ የቡና ሱሰኛን አምሮት የታደገ ካፌን አይቼ አላውቅም ትላለህ? እኔ ባለቤቱ የምናገረው እንዴት አይታመንም? የውብሸት መስፍንን “ሮሃ ካፌ” የማያውቅ ባለቅኔ ጥራ? ስንቱ ፀሐፊ ተውኔት ሮሃ ቁጭ ብሎ አይደል እንዴ ሀሳቡን ያረቀቀው? “ንጋት በጎንደር” የሚባለውን ተውኔት የት የተጻፈ መሠለህ? ሮሃ ካፌ ቁጭ ብሎ ፥ የሮሃ ካፌን ቡናን ትኩስ ትኩስን እየላፈ አይደለም እንዴ? እንዲህ መካካድ ምን ይሠራል!?”

ወጣቱ ለውብሸት መልስ ሳይሰጥ በዝምታ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋል የጠጣበትን የሻይ ሂሳብ የስኒው ማስቀመጫ ላይ ትቶ እየተጣደፈ ሄደ። በሁለቱ ካፌዎች በረንዳ ላይ ደርቶ የነበረው የቡና ጠጪዎች ሁካታ ጠፍቶ በዝምታ እና በሹክሹክታ ተተክቷል።

ብዙዎች መሳቅ ጀመሩ። የአራዳ ካፌ የአስተናጋጆች ሀላፊ ነጭ ሸርጡን አገልድሞ ውብሸትን ተጠጋው። ጠይም ረዥም ነው። ግራ ግንባሩ ላይ የሚታየው ከላይ ወደ ታች የተሠመረ የሚመስለው ጠባሳ የሆነ ዘመን ፈረስ እንደረገጠው ወይም በገጀራ ሳይፈነከት እንዳልቀረ ያስገምታል። ከለበሰው ነጭ ሸሚዝ ላይ አጠር ያለ የሥራ ኮት ደርቦ እጁን ለትህትና ወደ ኋላ አጣምሮ ቀረበ። ውብሸት ሞገስን ሲያይ እንደመረጋጋት አለ።

“ሞገስ አጅሬው። ኧረ ከዚህ ጉድ አውጣኝ፥ ካፌው ምን ገባ ይባላል” አለ ድምፁን ቀነስ አድርጎ።

ሞገስ ከዚህ በፊት ዐይቶት የማያውቀው ሰውዬ እንደ ቅርብ ወዳጅ አጅሬው ሲለው ተገርሞ

“ምን እንርዳዎ ጌታው፥ ደንበኞችን እያወኩ ነው?” አለ።

“ሞገስ!” አለ ውብሸት ድምፁን ከፍ አድርጎ። በንዴት እጆቹን እያጨበጨበ። “ሞገስ አንተም!ሞገስ…!”

“ያውቁኝ ኖሯል?”

“እንዴ ነኝና ውብሸት መስፍን ዘ–ብሔረ ሐረር! ያውቁኝ ነበር ይላል ይሄ!?”።

ሞገስ ግራ የገባው መስሎ በርጋታ ሁኔታውን ለመረዳት ውብሸትን ከዚህ በፊት ያገኘበትን አጋጣሚ ለማስታወስ የአእምሮውን ጓዳ መፈተሽ ጀመረ። ምንም ትዝ ሊለው አልቻለም።

“አንተም እንደማታውቀኝ ኾንክ?”

“እኔ ያለዛሬ አይቼዎት አላውቅም?”

“ይልቅ ቀልዱን ተውና ካፌዬ የት እንደሄደ ንገረኝ?”

“የቱ ካፌ?”

“ሮሃ ካፌ?”

“የምን ሮሃ ካፌ ነው ደግሞ ! ከሜክሲኮ አደባባይ እስከ ፒያሳ ድረስ ያሉትን ካፌዎች አብጠርጥሬ አውቃለሁ ፤ ሮሃ የሚባል ካፌ የለም ጌታው።”

“ምን ሩቅ አስኬደህ እዚህ በአራዳና ሸገር ካፌ መካከል ስንት አመት ሙሉ የኖረ ካፌ አላየሁም ስትል እንደው እግዜር አይታዘብህም?”

“ካፌው ቢኖር የት ይሄዳል ጌታው?ነፋስ አይደል?”

“አንተ ሞገስም አይደለህ”

“ልክ ብለዋል’

“የዛሬ ሁለት ወር ከሃያ ቀን ልጅ ስትወልድ ምን የመሰለ አሻንጉሊት ቤትህ ድረስ አላመጣሁልህም?”

“በርግጥ ልጅ ወልጃለሁ! የት ያውቁኝና ነው አሻንጉሊት ለልጄ የሚያመጡልኝ?”

ውብሸት ተናደደ። “የት ያውቁኛል፥ የት ያውቁኛል? ትላለህ ደግሞ! ስንት ቀን ደመወዝ አልደረሰም ፥ወር መድረስ አልቻልኩም ፥ ውብሸት አበድረኝ ስትል፥ ያለኝን እየመዠረጥኩ አልሰጠሁኽም?”

ሞገስ ብዙም ሳይናደድ “ጌታዬ የት ነበረ ካፌው ያሉኝ?”።

ውብሸት ቀና ብሎ ወደ ሁለቱ ካፌዎች ተመለከተ። ቡና የሚጠጣው ታዳሚም እየተንሾካሾከ የሁለቱን ምልልስ በትኩረት ያዳምጣል።

“እዚህ ነዋ” አለና ጎን ለጎን ኹነው ደንበኞቻቸውን ወደ ሚያስተናግዱት ካፌዎች ጠቆመ። “በሁለቱ መካከል ነዋ። ከአራዳ ቀጥሎ “ሮሃ” ከዚያ ሸገር ካፌ አልነበር የነበረው?” ሞገስ ሳቁን ላለመልቀቅ ሲታገል የሸገር ካፌ ባለቤት ግርግሩን ሰምቶ ወደ እነ ውብሸት ተጠጋ።

“ ጌታው እየረበሹ ነው አካባቢውን”

“ከካፌዬ ወዴት ልሂድልህ?” ውብሸት በንዴት እየጮኸ።

ሚሊዮን መነጸሩን አወለቀና ውብሸትን መረመረው።

“አቶ ሚሊዮን አንተም አላውቅህም እንዳትለኝ ብቻ?” አለ ውብሸት።

“ኧረ እንደውም!”

“ሮሃ ካፌን ስንት ዘመን ያስተዳደርኩትን ሰውዬ እንዴት ትዘነጋኛለህ?”

“ የምን ካፌ ነው?”

“የምን ካፌ ነው ይላል እንዴ ደግሞ! ይህም ካፌ ኾኖ ዘጥ ዘጥ ሲባልልኝ ተኑሯል። አላውቅህምና ነው ጫት ስትቸረችር፥ ምን እንደማታውቀኝ ትሆናለህ?”

ውብሸትን በሚጠይቁት ሰዎች ላይ ግራ መጋባት ይታያል። ውብሸትን ከዚህ በፊት ዐይተውት ባያውቁም፥ ስለእነርሱ መረጃዎች እንዳለው አውቀዋል። ሚሊዮን ጫት ንግድ ላይ የነበረው ዛሬ ሳይሆን የዛሬ ስንት ዘመን ነው። ዛሬ ሃያ ሁለት ማዞሪያ አካባቢ የኪነጥቡብ ሰዎች ጫት የሚቅሙበት ቤት ብቻ አለው።

" የት ነበር ነው የሚሉት ሮሃ ካፌ?"

"ስንት ጊዜ ልንገራችሁ ፥ እዚህ ነበር በሁለቱ ካፌዎች መካከል ፥ እናንተም ረስታችሁኝ ቁጭ አላችሁ እንጂ በአንድ ቀን አዳር፥ ምን ይደረግ ሲያመጣው!"

"መቼ"

"ትላንት ማታ ከምሽቱ አምስት ሠዓት ድረስ"

"እና የት ሄደ ?"

"ምን አውቃለሁ"

"መቼም ተነቅሎ አይጠፋ ነገር" አለ ሞገስ።

ውብሸት ተናደደ።

"ቢኖር የት ይሄዳል ፥ መቼም ካፌው ተነስቶ አይበር? " አለ ሚሊዮን ወደ ካፌው ለመግባት ፊቱን እያዞረ። ሞገስም ተከተለው። ውብሸትን በቆመበት ትተው ወደ ሥራቸው ተመለሱ።

የቡና ጠጪው ዐይን እርሱ ላይ አርፏል። ዐይኑን መልሶ ወደ ካፌዎቹ ላከ። እንዴት በአንድ ቀን ውስጥ እነዚህ ሁሉ ሰዎች ሊረሱት ፥ ሮሃ ካፌ ሊጠፋ እንደቻለ ፈፅሞ ሊገባው አልቻለም። 'በሕልሜ ነው እንዴ?' አለው ራሱን፥ በፍፁም በሕልሙ አይደለም። ሮሃ ካፌ የለም። ቀና ሲል ዐይኖች ሁሉ እርሱ ላይ ተተክለዋል።የተወሰኑት በሀዘኔታ ያዩታል።

"ምን ታፈጣላችሁ ፥ ምን ሁልሽም እንደማታውቂኝ ትሆኛለሽ?" ብሎ ድምፁን ከፍ ተናገረ። የመለሰለት አልነበረም።

"አንተ፥ አንተ" አለ ጥግ ላይ የሚያማስለውን ማኪያቶ እያየ ወተት እንደበዛው እያማረረ ወደነበረ አጭር ቦርጫም ሰው እየጠቆመ።

"አንተ አሁን አታውቀኝም፥ አንተ የሮሃ ካፌ የማኪያቶ ደንበኛ አልነበርክም?"

"ማ እኔ?" አለ ሰውየው

"እህሳ አንተ ራሥህ?"

"ሰውዬ ነገር አታምጣ ፥ የምን ሮሃ ነው 'ምታወራው፥እዚያ የእብዶች ሆስፒታል ጀምረው ይለቋችኋል። እዚህ መከራ ታበላላችሁ"

“ማን ነው እብድ አንተ” አለ ውብሸት ድምፁን ከፍ አድርጎ። “ማንም ላርጋቲን ሲግትህ አናውቅም እንዴ?” አለው።

ሰውዬው ደነገጠ።

“ሠላይ ነህ መሰለኝ። ምስጢራችንን ተሸክመህ የምትዞር ትመስላለህ። አሁን ነገር አትፈልገኝ።” ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀው ሰው እንዴት ስለእርሱ የአእምሮ ሕመም ሊነግረው እንደቻለ እያሰበ ማኪያቶውን እያማሠለ ዝም አለ።

ሞገስ በረንዳ ላይ ያለውን ጩኸት ሰምቶ ወደ ውጭ ወጣ። ውብሸት ከደንበኛ ጋር ሲነታረክ ደረሰ።

“ሰውዬ የንግድ ቦታ እየረበሹ ነው። ካልኾነ ፖሊስ ልጠራ ነው። ጣቢያው ሩቅ አይምሰልዎ…”

“ይምጣ ሺህ ፖሊስ ፥ ካፌዬን ነው የጠየቅሁ” አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ። “የሰው ካፌ መሰለህ፥ የራሴን ካፌ ፥ላቤን ነው ያልኩህ፥ ውብሸት መስፍን ዘብሔረ ሐረር ፥ለማንም የማይበገር ገጣሚ፥ ባለቅኔ። የሰው ቁራጭ ቁርጥራጭ ሳንቲም የምሻ እንዳይመስልህ” እያለ ወደ ሞገስ እየቀረበ መጣ። ሞገስም ወደ ኋላው እንደማፈግፈግ እያለ ነው።

“ፖሊስ እንዳልጠራ” አለ ሞገስ በድጋሚ እያስጠነቀቀ።

“ጥራ ሺ ፖሊስ፥ ዘብሔረ ሀረር። ማን ይፈራል ሞት። …ፖሊስ ትላለህ …ቂ…ቂ….ቂ ።… ደግሞ ለፈሳም ፖሊስ…”

የውብሸትን ትዕይንት ሲመለከቱ የነበሩ ሰዎች ጭቅጭቁ እየገረማቸውም፥ እያተከታቸውም ፥ አንዳንዶቹ ሂሳባቸውን እየከፈሉ እየሄዱ፥ አዲስ ቡና ጠጪዎች በቦታቸው እየተተኩ ነው።

ውብሸት ሞገስን አልፎ እየተንደረደረ ወደ አራዳ ካፌ መታጠቢያ ቤት ሄደ። በካፌው ውስጥ እያውካኩ ቡናቸውን የሚጠጡ ደንበኞች ውጭ ምን እንደተፈጠረ ስላላስተዋሉ የውብሸት እየተጣደፈ ወደ መታጠቢያ ቤት መሄድ ብዙም ትኩረት አልሰጡትም። ትኩረታቸው ወደ ውብሸት የተሳበው፤ “ሰውዬ ውጣ” እያለ ሞገስ ሲከተለው ነው።

“ሽንቴን ልሽናበት” እያለ መታጠቢያ ቤቱን ከውስጥ ቆለፈው። እነ ሞገስ የመታጠቢያ ቤቱ በር ላይ ቆመው ሲንሾካሾኩ ይሰማዋል።

ከመታጠቢይው ፊት ለፊት ሲደርስ ዐይኑን ጨፈነ። ራሱን ከመታጠቢያው ፊት ለፊት ባለው መስታወት ራሱን ላለማየት እየፈራ ተጠጋ። ሌላ ሰው ሆኖ ቢያገኘው ራሱን የማን ያለህ ሊል ነው ?ዐይኖቹን ጨፍኖ

ቧንቧውን ከፈተው። ውሃው በእጆቹ ላይ ሲፈሱ ተሰማው። በረጠበ እጆቹ በላብ የወረዛውን ፊቱን በመዳፉ አበሰው። የጨፈናቸውን ዐይኖቹን እንደምንም ገለጠ። ራሱ ነው።

በእርግጥ ዋናው  ውብሸት መስፍን ነው እንዲህ የሚደርስበት?ወይስ ነፍሱ ከእርሱ ተነጥላ አንድ ሌላ የማያውቀው ሰው ውስጥ አድራ ነው? ወይስ አልነቃም ከእንቅልፉ ? የኢየሩሳሌምን ጥፋት አታሳየኝ ብሎ ስልሳ ስድስት ዓመት በእንቅልፍ ያሳለፈው የነቢዩ ኤርሚያስ ወዳጅ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ት ዝ አለውና ምን አልባት እርሱም ስልሳ ዓመት ወይም ያነሰ ጊዜ ተኝቶ ሳይነቃ ከርሞ እንደኾነ ጠረጠረ። ይህ ሁሉ ዘመን ተኝቶ ከእንቅልፉ ሲነቃ የባሰ ጃጅቶ እንዳይሆን እየፈራ ጉዱን ለማየት ዐይኖቹን ገለጠ። ያው ነው። ራሱ ውብሸት መስፍን። ፊቱን በመዳፉ ጨመቀው።

ትላንት የሚያስታውሰው ውብሸት መስፍን ነው።  ፀጉሩን ሽበት ወርሮታል።  የግንባሩ ቆዳ መስመር እየሠራ መሸብሸብ ጀምሯል።   ዐይኖቹ የግራ ቅንድቡ ላይ አረፉ።  ከቀኝ ቅንድቡ የበለጠ ነጭ ፀጉር በዝቶባቸዋል። የግራ እጁን ጣቶች ሠድዶ ቅንድቡን በረጠቡ ጣቶቹ ዳሠሳቸው። ዛሬ ሥለ ቅንድቡ መሸበት የሚጨነቅበት ቀን አይደለም። ላለፉት አሥራ አምስት አመታት ሲያስተዳድረው የኖረው ካፌ እምጥ ይግባ ስምጥ ሳይታወቅ የጠፋበት ሠዓት ነው። የሚያውቁት ሰዎች እንኳን ሊያናግሩት ፈቃደኛ ሳይሆኑ እያዩ እንዳላዩ ሲያልፉት ተመልክቷል።
ሞገስ ከውጭ በኩል ሆኖ “ወጣልኝ አንተ ሰውዬ ፖሊስ እንዳልጠራ፥  በኋላ ለምን ጣቢያ ወሬ ላላ ተገለበጥኩ እንዳትል?” እያለ ሲናገር ይሰማዋል።
“ሮሃ ካፌ ሮሃ ካፌ የት ገባ?” አለና መስታወቱ ውስጥ የሚያየውን ሰው ጠየቀው።
* * *
ውብሸት ከትውልድ ከተማው ሀረር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ የሂሳብ ሠራተኛ ኾኖ ከተቀጠረበት ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እስከ ሮሃ ካፌ የደራ የየደመቁ ጊዚያት በዐይነ ሕሊናው ውልብ አሉ። ሌላ ምኞት አልነበረውም። ገጣሚ ፥ ባለቅኔ መኾን ብቻ ነበር የቀን የሌት ሕልሙ። ፈራሽ በስባሽ ሥጋ እንደለበሰ ሰው ሳይኾን፥ እንደ ታላቅ ባለቅኔ፥ ከሞት በላይ ፥ ከመረሳት በላይ መኾን ነበር የሚሻው። “...መኾን አለመኾን እሱ ላይ ነው ሚስጥሩ...” የምትል አንዲት ስንኝን ፈጥሮ ለዘላለም መሳፈር፥ እርሷ ላይ።   ስሙ በዓለም ሲጠራ፥ መጽሐፎቹ የትምህርት ቤት መማሪያ ሲኾኑ፥ የገጠማቸው ስንኞች በየሰው አንደበት የማይለዩ ሲኾኑ ቁጭ ብሎ ዘላለማዊ መኾንን ሲያልም ይውላል።  ግን የተሳካ ስንኝ ቋጥሮ የራሱንም፥ የጓደኞቹንም መንፈስ በግጥም ያረካበት ቀን ት ዝ አይለውም። የግጥም ውድድር አለ በተባለበት ሁሉ ለመወዳደር የፃፋቸውን ግጥሞች ይልካል። ያን ሁሉ ግጥም ልኮ አንድ ቀን እንኳን “ግጥምህ ደርሶናል” የሚል መልስ

አግኝቶ አያውቅም። አይታክተውም ግን። ሥራውንም ፥ ማሕበራዊ ሕይወቱንም እየበደለ ግጥም ሲያረቅ ይውላል።

ለሥነ ጥበብ ሥራው በቂ ጊዜ ለማግኘት በሚል ከፖስታ አገልግሎት ድርጅት ውስጥ የነበረውን ሥራ ለቅቆ ወንድሙ ጋ ድሬዳዋ ሄደ። ወንድሙ የኮንትሮ ባንድ ነጋዴ ነው። ዛሬ ያገኛል፤ ነገ ያጣል። ኑሮው እንዲያ ነው።
"ሥራህስ?" አለው ገና ውብሸትን ሲያየው።
"ተውኩት"
"ከእኔ ጋር ትነግዳለህ እንኳን መጣህ"
"ኮንትሮባንድ?'
"አርቲሼክ ማለዳ እንሄዳለን ተዘጋጅ" አለው። ውብሸት አቅማማ።
"አቦ አትነጅሰኝ! እኔ የመጣሁት የተወሰነ ጊዜ ከአንተ ጋር እየኖርኩ ግጥም ልፅፍ ነው"
"ማሽላ ጠባቂ አይደለህ አንተ ግጥም ምን ይሠራልኻል?"

ውብሸት ግን ሀሳቡ ቁርጥ ነበር።  ለሁለት ዓመት ወንድሙ ጋር እየኖረ  የግጥሙን ረቂቅ ሥራ ጨረሰ። እርሱ ድሬዳዋ ቁጭ ብሎ ወንድሙ ሮሃ የሚባል ካፌ አዲስ አበባ ላይ ከፈተ። ወደ አዲስ አበባ የተመለሰው የወንድሙ  ካፌ ለማስተዳደር እና በዚያውም ግጥሙን ራሱ ለማሳተም ነበር። ወንድሙ በባቡር አደጋ ሕይወቱ ካለፈ በኋላ ሮሃ ካፌን በስሙ አዛውሮ በባለቤትነት ያስተዳድረው ጀመረ። ከዚያ በኋላ ነው ሮሃ መታወቅ የጀመረችው።
* * *
መታጠቢያ ቤቱን ከፍቶ ወጣ።
"እዬ ሞገስ እንደማታውቀኝ ትሆን አንተ?" አለ ውብሸት ሞገስን በትዝብት እያየ።
"ማሪያምን አላውቅህም"
ውብሸት ከካፌው ወጥቶ በረንዳ ላይ ቆመ። ሮሃ ካፌ ግን የለም። የት ተሰወረ ካፌው?ፈጽሞ ሊረዳው አልቻለም።
የ "ሽገር" ካፌ ባለቤት ሚሊዮን ራቅ ብሎ ቆሞ "አገኙት ካፌውን?" አለ እንደማሾፍ አድርጎ። ውብሸት ሳይመልስለት አልፎት ሄደ። ከሁለቱ ካፌዎች እየራቀ ሲሄድ ልቡ በሀዘን ተሞልቶ፥ መንፈሱ ሊገልፀው በማይችል ግራ መጋባት ተወጥሮ ነበር።

የሚያውቁትን ሰዎች እየፈለገ ጉዳዩን ማስረዳት እንዳለበት ወሰነ።

ባለፉት አሥር ዓመታት ከብዙ የጥበብ ሰዎች ጋር ተቆራርጧል። አንዳንዶቹ ግን እስካሁን ያስታውሱታል። መጽሐፉን እያደነ እንደሚያቃጥል ስለተሰማ በተወሰኑት ዘንድ እንደሚታወቅ ይጠረጥራል። ቢያንስ ጉዳዩን የሚረዱት ሰዎች ያገኝ ይሆናል።

ከብሔራዊ ቲአትር ጀርባ ወደሚገኙ መጽሐፍት መሸጫ መደብሮች አመራ። በተለይ ከሻውል አሮጌ መጽሀፍ መሸጫ ሱቅ ባለቤት ጋር የከረመ እውቂያ አለው። ከሃምሳ በላይ የራሱን የግጥም መጽሀፉን ገዝቶ ያቃጠለው ከሻውል ሱቅ ገዝቶ ነው። የሱቁ ባለቤት በቃሉ መጽሀፍ ሲያስተካክል አገኘው። ውብሸት ለበቃሉ የሞቀ ሠላምታ ስጠው።

“በቃሉ ጀግናው፥ አደግሽ እኮ አይናችን እያየ”

በቃሉ ውብሸትን በግርምት አይን እያየ “እንደምን አረፈዱ” አለ ቅዝቅዝ ባለ መንፈስ።

“በቃሉ” አለ ውብሸት።

“አቤት” አለ በቃሉ ድንግር ብሎት።

“ኧረ የሆንኩትን ጉድ ስማ?” አለ ውብሸት በወዳጅነት መንፈስ። የበቃሉን መደናገር ሳያስተውል።

“ምንድን ነበር ጌታው?” አለ በቃሉ።

“እንዴ...” አለ ውብሸት፤ “አላውቅህም እንዳትለኝ ብቻ አንተም” አለ ሥጋት ብጤ አድሮበት። በቃሉ ፈገግ አለና “ይቅርታ ረስቼዎ ይሆን እንዴ?”አለ በቃሉ ደንበኛውን በመርሳቱ እንደማፈር እየለ። ውብሸት ለመረጋጋት ሞከረ። ወደ ሱቁ ጠጋ ተጠጋ።

“የገጣሚ ውብሸት መስፍን ‘የንጋት ወፍ ጥሪ’ የሚለው መጽሀፍ ይኖርኻል?”

በቃሉ ለማሰብ ሞከረ። ትዝ ሊለው አልቻለም።

“ይቅርታ እንዲህ የሚባል ገጣሚም ፥ መጽሀፍም ሰምቼ አላውቅም” አለ።

“ርግጠኛ ነህ?” አለ ውብሸት።

“ገብርኤልን”። ማለ።

“አታውቀኝም እኔን?” አለ ውብሸት። በቃሉ ፊት ለፊቱ የቆሙትን ሰው ለአፍታ አተኩሮ ሲያይ ቆየና።

“ከአሜሪካ ነው የመጡት” አለ እየተጠራጠረው ራሱን።

“አይተኸኝ አታውቅም?” አለ ውብሸት ። ወጣቱ መጽሐፍ ነጋዴ ራ ሱን በአሉታ ነቀነቀ።

“ታውቀኝ ነበር እኮ በቃሉ። ታውቀኝ ነበር። እሺ ሮሃ ካፌንም አታውቅ?”።

“የት ነው?”

“ብሔራዊ ቲአትር ሥር ነዋ፥ ስንት ቀን ቡና የጠጣህበትን”

በቃሉ ራሱን ነቀነቀ። ውብሸት መልስ ሳይጠብቅ እያጉረመረመ እንደሚያውቁት ወደ ተማመነባቸው ሶስት መጽሀፍ ሻጮች ጋር ሄደ። ተመሳሳይ ነገር ገጠመው። አያውቁትም። እርሱንም ÷ ካፌውንም የሚያውቀው ሰው አላገኘም። ርግጠኛ ነው። ትላንትና ማታ እዚህ አዲስ አበባ ላይ÷ ሮሃ ካፌን እያስተዳደረ÷ በነጭ ወረቀት ላይ ግጥም ለመግጠም ሲሞክር የኖረ ሰው ነው። ጎልውናው በአዋጅ የተሻረ ይመስል የሚያውቁት ሁሉ በአንድ ቀን ጀንበር ልዩነት ፈፀሞ ረስተውታል። ወደ ኪሱ ገባ እና መታወቂያውን ፈለገ። አየው። የውብሸት መስፍን 'ዞብሔረ ሀረር ÷ ለማንም የማይበገር' ፎቶ የያዘ መታወቂያውን አወጣ። ራሱ ነው። 'እንዴ! በሰው አእምሮ ውስጥ መታወስ ነውና ሕልውና ማለት?' አለ ለራሱ።

ንግድ ሥራ ኮሌጅ ጀርባ ወደ ሚገኘው ቴሌ ባር ሄዶ በረንዳ ላይ ተቀመጠ። ትላንት ማታ ወደ ቤት ከመሄዱ በፊት በፊት ያመሸው እዚህ ነበር። የብዙ አመት የብዙ አመት ደንበኛ ነው። የሚያውቀው አስተናጋጅ መጣ። አስተናጋጁም ፍፁም ረስቶታል። ቡና አዘዘ። አስተናጋጁ ቡናውን ይዞለት ሲመጣ ጉሮሮውን እያፀዳ "ይቅርታ ወንድሜ ሮሃ ካፌ የት እንደኾነ ታውቃለህ ?"አለ። አስተናጋጁ ራሱን ነቀንቆ ሄደ። ከእርሱ ጋር ሲሠሩ የኖሩ አስተናጋጆች የት እንደሄዱ አያስታውስም።

ከቴሌ ባር ወጥቶ ጎያሲና ጠበቃ ማሩ ቢሮ ወደሚገኝበት ቴዎድሮስ አደባባይ እየተጣደፈ ወጣ። ማሩ ሊያስታውሰው እንደሚችል ተስፋ አድርጓል። አካባቢውን እያስተዋለ በሀሳብ ተውጦ የቸርቸል ጎዳናን ዳገት ይወዘወዘው ጀመር። በምን ምክንያት ይህ ነገር ሊደርስበት እንደቻለ ፈፅሞ ሊገባው አልቻለም። ጊዜ ካለፈ ተወልዶ ነው እንዳይል÷ ትላንትና ማታ ከነበረው አንድ ነገር እንኳን አልተቀየረም። የተቀየረው የእርሱ አሻራ በሙሉ መሠረዙና÷ እርሱም በሚያውቃቸው ሰዎች ጎሊና ውስጥ ሙሉ በሙሉ መፋቁ ነው። ካፌውስ የት ሄደ ይባላል ግዑዙ ነገር? የግጥም መጽሐፉን ሰብስቦ ሲያቃጥል የነበረው እንደገጣሚ እንዲረሳ እንጂ እንደሰው ሙሉ በሙሉ እንዲዘነጋ አልነበረም እኮ።

ጎያሲ ማሩ ቢሮ ደረሰ። ሮሃ ካፌ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የማይጠፋ ደንበኛው ነበር። መጽሐፉ ላይ የሠጠው ልብ የሚሠብር ጊስ ግንኙነታቸው እንደቀድሞ እንዲሆን አላስቻለውም። ብዙዎች ሮሃን ጥለው ሲጠፉ ጎያሲ ማሩ ግን አልፎ አልፎ ብቅ እያለ በዝምታ ቡናውን ጠጥቶ ይወጣል።

ከሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ከፍ ብሎ ወደ ሚገኘው የማሩ ቢሮ ደረሰ። የቢሮውን በር አንኳኩቶ ወደ ውስጥ ገባ። እንግዳ ተቀባይዋ እንዲጠብቅ ነገረቻው። ከአፍታ ቆይታ በኋላ ወደ ማሩ ቢሮ እንዲገባ

ተጋበዘ። ማሩ ከመቀመጫው ተነስቶ ተቀበለው። ወዳጁን ሠላም በሚል ሳይሆን፥ ደንበኛው በሚቀበል ት ሕትና።

“ማሩ” አለ ውብሸት።

“አቤት” አለ ፈገግ ብሎ ጎያሲው በጎርናና ድምፁ።

“እስኪ የምርህን ሳትደብቅ ንገረኝ?” አለ።

“ምን ልንገርህ?”

“አታውቀኝም እንዴ?” ማሩ የውብሸትን ፊት እያየ ለማስታዋል ሞከረ። አሰበ።

ራሱን ነቀነቀ። “ይቅርታ ጌታዬ ረስቼዎታለሁ መሰል” አለ።

“ደራሲ ነበሩ?” ጠየቀ ጎያሲው።

“ሮሃ ካፌ፥ ብሔራዊ ቲአትር ስር ስንት ዘመን ስትመላለስበት የኖርከውን ካፌንስ ታስታውሰዋለህ?” አለ ውብሸት”።

“ብሔራዊ ቲአትር ሥር? ኖ.. ኖ! እንዲህ የሚባል ካፌ ት ዝ አይለኝም።”

ውብሸት የሚሰማውን ነገር ማመን አልቻለም።

“አንተም አታውቀኝም እንዴ ማሩ ወዳጄ ፥ ምን ጉድ ገባሁ፥ ‘የንጋት ወፍ ጥሪ’ የሚባል የግጥም መድብልስ አታውቅም?”

ራሱን ነቀነቀ ማሩ። ከውብሸት ጀርባ ወደ ተደረደሩት መጽሐፍት እየጠቆመው።

“እስከዛሬ ሂስ የጻፍኩባቸው ሥራዎች በሙሉ እዚህ መደርደሪያ ውስጥ አስቀምጣቸዋለሁ። ማየት ነው። ያንተን የግጥም ሥራ አላውቀውም። ይቅርታ።”

ውብሸት ተነሳ። እጅ ነስቶ ከማሩ ቢሮ ወጥቶ ወደ ብሔራዊ ቲአትር ተመለሰ። ሮሃ ካፌ የለም። ቀኑን ሙሉ ምሳም፥ቁርስም አልበላም። ምን ዋጋ አለው መብላት።

የግጥም ምሽቱ ፕሮግራም ሊደረግ ሶስት ሠዓት ይቀረዋል። ብሔራዊ ቲአትር ፊት ለፊት ቆሞ ወደ ሮሃ ካፌ ለመግባት ሊመጡ የሚችሉ የጥበብ ሰዎችን ሲጠብቅ ቆየ። ሠዓቱ እየከነፈ ነው።

አንድ ሠዓት ቀረ።

ሠላሳ ደቂቃ።

ዐይኖቹን አሻግሮ ሮሃ ካፌ እስከ ትላንት ማታ ድረስ ወደነበረበት ቦታ ይወረውራል። የሸገርና የአራዳ ካፌ ደንበኞች ይገባሉ ይወጣሉ። ሮሃን ያስታወሳት የለም። እርሱም ምድር ላይ ኖሮ የማያውቅ ይመስል ፈፅሞ ተዘንግቷል።

ሠዓቱ ደረሰ።

ወደ ሮሃ የመጣ አንድም ሰው የለም። ሮሃ ካፌም በቦታው የለችም።

እያዘነ ፥ ግራ በገባው መንፈስ ላለፉት አስራአምስት አመት ሲሰራበት የቆየውን ሮሃን ካፌ ለቅቆ ወደ ስታዲየም አቅጣጫ ሄደ። የሚያውቀው ሰው በዐይኑ ይፈልጋል። እርሱ የሚያውቃቸው እንጂ የሚያውቁት ሰዎች ሊያገኝ አልቻለም። ከአዲስ አበባ ስታዲየም የሚወጣ የእግር ኳስ ደጋፊዎች ዜማ አካባቢውን ሞቅ ደመቅ አርጎታል። ስታዲየሙን ትቶ ወደ አብዮት አደባባይ የሚወስደውን መንገድ ይዞ መራመድ ጀመረ።

መጽሀፍ የተሸከመ ወጣት ከፊት ለፊቱ መጣ። "ያለቀበት ያለቀበት" እያለ መጽሐፉን ለመሸጥ ይሞክራል።
"ስማ አንተ 'የንጋት ወፍ ጥሪ' የሚል የግጥም መጽሀፍ ይዘሃል?" አለ ውብሸት።
መጽሀፍ ሻጩ ውብሸትን እያየ በሳቅ መንከትከት ያዘ።
"...ሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻ.."
ውብሸት ለምን እንደሚስቅ አልገባውም።
"ይዘሃል የታዋቂውን ባለቅኔ መጽሐፍ" አለ ። "የባለቅኔ ውብሸት መስፍንን መጽሐፍ..."ደገመ
የመጽሐፍ ሻጩ ሳቅ አላቆመመ።
"...ሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻሻ..."
"የባለቅኔ ውብሸት መስፍንን መጽሐፍ..." ደገመ።
ውብሸት ሳቁን ላለመስማት ጆሮውን ሸፍኖ መንገዱን አፈስ አፈስ እያደረገ ወደ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ ገሰገሰ። ወዴት እንደሚሄድም ርግጠኛ አይደለም። ቤተ ክርስቲያኑን አልፎ ቁልቁለቱን በርጋታ ከወረደ በኋላ ወደ ድልድዩ ተጠግቶ ቆመ።

ዐይኖቹን በድልድዩ ሥር ወደሚፈሰው በበጋ ፀሐይ የተዳከመ ወንዝ ላይ ተክሎ ቆየ። ጅረቱ በወንዙ ድንጋዮች መካከል እየተስለከለከ ይፈሳል። እየጨለመ ነው። ጨለማው ቀጭኑን ጅረት እየሸፈነው ነበር።